# ለራስ የተጻፈ ደብዳቤ

## (የብርሃን ፍቅር ቅጽ 2)



ከደበበ ሠይፉ

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# ለራስ የተፃፈ ደብዳቤ

(የብርሃን ፍቅር ቅጽ ፪)

በደበበ ሠይፉ

1992

# ማውጫ

**ርዕስ**......**ገጽ**


መግቢያ ........ 4
ሙሉዋ ጨረቃ ........ 6
አደን ........ 7
በመንፈቅ ሌሊት ........ 8
ለምን ለምን..... ........ 9
ጠብቄሽ ነበረ........ 10
ሂጂ በይ፤......ደህና ሁኚ........ 11
ሔዋን ብቻ ለአዳም........ 12
ባይታይህ ኮከቤ........ 14
የተስፋዬ ዛፉ ........ 15
ሥጋ ብቻ ለሰው ........ 16
ድንቁርናችንን ይቅር በለው ........ 17
ውበት ባትከፋ ........ 18
ቅዠት......ቅዠት ........ 19
ብቅ በይ ጣይቱ........ 22
ወጣ በይ ጣይቱ። ........ 23
"እ ና"........ 24
ለራሴ ባላሁት........ 25
በደል........ 25
ሀምሳ እግር........ 26
ባለ አደራ........ 27
እኔና ጨረቃ........ 28
እኮ ልብን እንዴት ያገስጿል?........ 28
አጸለሌ........ 31
ተይ አይሆንም ነብሴ ........ 34
ለራስ የተጻፈ ደብዳቤ ........ 35
እኔ ሆይ ተጠየቅ ........ 46
ሰብአ ትካት ........ 46
ከአክሱም ጫፍ አቁማዳ........ 49
ጥናቱን ይስጥሽ እማማ ........ 53

ውቢት ........ 55
በለስ ለመለመች ........ 57
አይ መባከን ........ 58
ጉልበቴ በርታ፣ በርታ ........ 61
ለምን ሞተ ቢሉ ........ 62
ይቅርታ ለይቅርታ ........ 63
የቋንቋ ሊቆቼ ........ 64
በመላ ዕድሜያቸው ........ 65
ለአንዲት ቅጽበት ብቻ ........ 66
ያላዋቂ ጠያቂ ........ 66
ከያኒና ኪነት ........ 67
በተረት ላሰላስል ........ 70
ባለቅኔዎች - (ከሎንግፌሎ የተተረጎመ) ........ 72
ኒሻን ........ 74
መንገደኛ ........ 75
ተይው እንተወው ........ 77
ብቻ ለሚያንሾካሹከው ........ 78
አባብዬ ........ 79
የክረምት ማገዶች ........ 80
አይደለም (የዘወትር ምጤ) ........ 81
ጊዜ በረርክ በረርክ ........ 81

# መግቢያ

ደበበ ሠይፉ ሐምሌ 5 ቀን 1942 በይርጋለም ከተማ ተወለደ። የአንደኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በይርጋዓለምና በአዲስ አበባ ከተማ ኮከበ ጽባሕ ት/ቤቶች ከተከታተለ በኋላ አዲስ አበባ ዩኒቨሲቲ ገብቶ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ የባችለር ድግሪውን፤ በእንግሊዝኛ ሥነ ጽሑፍ የማስትሬት ድግሪውን ተቀብሏል።

ደበበ ሠይፉ የመጀመሪያ ድግሪውን በማዕረግ እንደተቀበለ ከ1966 ጀምሮ እስከ 1985 ድረስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመምህርነት እና በረዳት ፕሮፌሰርነት ማዕረግ አገግሏል።

ደበበ ሠይፉ እጅጉን በገጣሚነቱ የሚታወቅ ቢሆንም ጸሐፊ ተውኔት፤ ተርጓሚ እና የምርምር ባለሙያ ነው። የተወሰኑት ተውኔቶች በልዩ ልዩ መድረኮች ቀርበዋል። «የቲያትር ጥበብ ከጸሕፊ ተውኔት አንፃር» በሚል ርዕስ ያዘጋጀው መጽሐፍ ታትሞለታል። ቀደምት የግጥም ሥራዎቹን የያዘ «የብርሃን ፍቅር ቅጽ ፩» በሚል ርዕስ አሳትሟል። ይኸኛው የግጥም መጽሐፉ ደግሞ ቅጽ ፪ መሆኑ ነው። ደበበ በግጥም ችሎታው፤ በይዘት አመራረጡ፤ በቃላት አጠቃቀሙ ብዙ ሊባልለት የሚችል ገጣሚ ቢሆንም በዚህ አጭር መግቢያ ስለ ግጥሞቹ መግለጫዎች መስጠት ያስቸግር ይሆና። ቢሆንም.......

ደበበ ሠይፉ በርእስ አመራረጥና በሚያስተላልፋቸው ልብ የሚነኩ መልዕክቶች ብቻ ሳይሆን በስንኞቹ አወራረድ፤ በዜማና በቤት አመታቱ በአጠቃላይ በውብ አቀራረቡ ተደራሲያንን የሚመስጥ ገጣሚ ነው። ስለ ተፈጥሮ ሲገጥም ፀሐይና ጨረቃ፤ ቀስተ ደመናና የገደል ማሚቶ ያጁብታል። ስለ ፍቅር ስንኞች ሲቋጥር የፍቅረኞችን ልብ እንደ ስእል ቀንጆ አድርጎ በቃላት ቀለማት ያሳያል። ክህደት ላይ እንደ አንዳንድ ገጣምያን አያላዝንም። ይልቁንም ውበትና ህይወትን አገናዝቦ «ያውላችሁ ስሙት፤ እዩት» ማለትን ይመርጣል ፡

ደበበ ቃልት በጁ ናቸው። ሆኖም እንደ መጡለትና እንዳሰኘው አይለቅማቸውም። ጥሩዎቹን በጥሩ ቦታቸው በአዕምሮው እያማጠ መርጦ ያሳካቸዋል። ምስል ፈጠራው ለምናብ ተስማሚና አመርቂ ነው። በደልን አስመልክቶ ከጻፈ በደል በወፋፍራም እጆቹ ያነቃችሁ እስኪመስላችሁ ድረስ ይዘገንናችኋል። የሕይወትን አስገራሚ ጉዞ «እይ መባከን» ይለዋል። እኛነታችንን ሲያሳየን «ለራስ

የተጻፈ ደብዳቤ» ያስነብበናል። «እንኳን በቃኝ» ሲለን ደግሞ እውነትና ሰንካላነት በፈጠጠ ቋንቋው ይነግረናል ፡

ሳቅና ለቅሶን፤ ዕውቀትና ድንቁርናን፣ እርግማንና ምርቃትን እና የመሳሰሉትን አዋህዶም ቃርኖም በስድ ንባብ ሊባል የሚያስቸግራቸውን ሁሉ በስሜትና በውበት ወጥሮ ማስነበብ በተሰጥኦ መታደል ይመስለኛል። ለሀገሩ ተቆርቋሪነቱን በኪናዊ ዘዴ የሚናገር ደራሲ የወገኖቹን ሰቆቃ ከኑሮው፣ ከባህሉና ከልማዱ ጋ አያይዞ ሲያቀርብ ኪነቱን ለእውነት ማራመጃ አዋለው ማለት ነው። ደበበ የነዚህ ሁሉ ባለቤት ነው። «እዋይ» ን ሲያነሳ የማኅበራዊ ሕይወት ቋንቋ ያደርጋታል። «ከዘመን ጋር ተኳረፍኩ» ቢልም በአገባጠም ብልሃቱ በኩርፊያው ውስጥ ስውር ተስፋን ያስተጋባል።

እኔ እንደማውቀው ደበበ ሠይፉ በገጣሚነቱ ሁሌም ዝምተኛ ነው። አይጮህም። ጮሆም አያስበረግግም። ይልቁንስ ደጋግመን እንድናነብለት የሚያደርገንም ይኸው ችሎታው ነው። ለሱ ውበት ማለት ሰማዩና ምድሩ ብቻ አይደሉም። ዋናው ምሰሶው ሰው ይመስለኛል - የሰው ፍቅር። በብዙ ግጥሞቹ ይኸ ጎልቶ ሲወጣ አይቻለሁ።

.....ለማጠቃለል ደበበ ሠይፉ የግጥም ባህላችንን በእጅጉ ያዳበረ ገጣሚ ነው ብዬ አምናለሁ።

መስፍን ሀብተማርያም

# ሙሉዋ ጨረቃ

ሙሉዋ ጨረቃ

ብሩህ ነሽ ደማቃ

ታለቅሣለች ነብሴ ተስፋ ትቆርጥና

በውበትሽ ተማርካ በመራቅሽ አዝና፤

ብሆን ከወለሉ አንችም ጣርያ ላይ

ዝቅዝቅ ከሚያዩትስ እሚያምር የለም ወይ?

አንተን ሲያቀኑ ብቻ ነው ማማሩ

ያም ይኼም ያም ይኼም ዐይንን ማጭበርበሩ

ፈክቶ መታየቱ ሽልምልም ማለቱ

በሩቅ ማጓጓቱ?

ለዐይንም ሌላ ዐይን አለው

አንድን ጥርኝ አፈር

ድንጋይ ብሎ እሚያስጥል በየጉራንጉሩ

ወርቅ ብሎ የሚያስቋጥር በየማህደሩ።

እኔውም ብሆን ነው የዐይኔ ዐይን ባርያ

ሣውቀው መሆንሽን የሌሎች አምሣያ

ጉልላት ያረኩሽ የፍጥረት አናት

በውን እምትሞቂ ድንቅ የሕልም እሣት።

ዳኛ ነው የሚፈርድ ምክንያት ጠቅሶ መጽሐፍ አንብቦ

ግን ከሣሽ ተከሣሽ (ያው እንደኔ እንዳንቺው)

ስሜቱን አንግቦ

አእምሮው ረግቦ።

አውቃለሁ እንዳይሽ ይህ ብሉይ ዐዋጅ

ከአለኝታዬ አይጃጅ በምኞቴ አይዋጅ

እንደነበር ሊኖር መታከት......መታከት.......

መታከት ነው እንጅ

ነውናም ስገብር ለዐዋጅ ለዕጣዬ

‹አንቺ ዝቅ ብለሽ ወይ እኔ ከፍ ብዬ

እንገናኝ ይሆን?›....ሆኗል ጥያቄዬ።

# አደን

አሣድጄን አመለጥኳት

አመለጠችኝ ያሣደድኳት።

ኗሪ ሆንኩኝ እንደ ፍየል

በነብርና ቅጠል መሀል።

አቤት አለች ያልጠራኋት

የጠራኋት ድምፅም አላት።

ራቂኝ ‹ምላት ጎኔ ወድቃ

ቅረቢኝ ‹ምላት ከኔ ርቃ።

አንዴ ስታደን አንዴም ሳድን

ዕረፍት አጥቼ ስባክን

የዕድሜዬን ጀንበር ብታዛባት

ልትጠልቅ ምንም አልቀራት።

# በመንፈቅ ሌሊት

ከቶ ግድ የለኝም

አያሳስበኝም

የሆነው ሳይሆን

ያልሆነው ቢሆን

......ሁሉም

ሌላው ሁሉም፤

ባይጣፍጥ ባይጥም፤

ፍሬሽ ቢሆንብኝ

እጅግ አማሳኝ

መቼ ግድ አለኝ?

ላንቺ እንጂ መድከሜ

መድቀቅ መታመሜ

ምኔም መባዘኔ

ፍስሐዬ ለኔ።

እንደ ዓይኔ......እንደጣቴ

እንደው እንደ ፍጥረቴ

ተቀብዬሻለሁ በሰራ አካላቴ።

አንችዬ የኔ ነሽ

እኔም የምንጊዜሽ

ዕድሌ የሰጠኝ

ዕጣሽ የለገሰሽ።

# ለምን ለምን.....

ነፋሱ ሣር ቅጠሉን አዋከበው

ሞገዱ፤ ባሕሩን አናወጠው

ግን የኔን ልብ ምን አራደው?

ምንም የለ ‹ሚታወሰኝ

ድንገት እንጅ ሆድ የባሰኝ።

ለምን አልኩኝ ተጨብጨ

እንባዬን ባፌ መጥጨ

ሳውቅ ጥያቄ መልስ እንዳይሆን

የለምን ለመን ለምን ሊሆ?!

# ጠብቄሽ ነበረ

መንፈሴን አንጽቼ

ገላዬን አጥርቼ

አበባ አሳብቤ

አዱኛ ሰብስቤ

ጠብቄሽ ነበረ፤

ብትቀሪ ጊዜ፤

መንፈሴን አሳደፍኩ

ገላዬን አጎደፍኩ

አበባው ደረቀ

አፉኛው አለቀ፤

ብትቀኢ ጊዜ፤

የጣልኩሽ ተስፋ

እኔን ይዞ ጠፋ።

# ሂጂ በይ፤......ደህና ሁኚ

ፍቅሬ አስጠልቶሻል፤

እጅ እጅ ብሎሻል፤

ተቆልቶ ጠንዝቶ ቃናውም መሮሻል።

ከቶ አላግድሽም፤

ሂጅ......በይ ደህና ሁኚ፤

የፍቅር አሡሩን እኔም አልመኚ።

«ቅዱስ ነው እማዬ፤

እሱን ካላገባሁ ደርሷል መሞቻዬ፤

እህል ከተባለ ይፁም ጉሮሮዬ......»

........ስትይ የሰሙ እህት እናትሽ፤

እንዴት ይታዘቡሽ በዛሬው ቃልሽ?

«ሰይጣን ነው እሱ

ያውም ልክስክሱ፤

ሁለተኛ እግሮቹ ተደጁም

አይደርሱ.....»

......ደሞም ሰማሁ እንዳልሽ፤

«ትዳር ነው ማለት፤

ወህኒ.....እግር ብረት፤

ገራገሩ ሴቶች ‹የሚጠፈሩበት።

ሰው ሊበር ይችላል ያላንዳች ሀሣብ፤

ከፈለገው አርፎ ሊቀስም እንደንብ።......»

ደህና.....ምን ቸገረኝ።

ንብ ሁኚ፤

ዝንብ ሁኚ፤

ቢራቢሮ ሁኚ፤

አንዴ እንደሆን ለኔ ሰው አልመሠልሽ።

.....የነደልሽው ቤቱን ጭራሽ ሣታፈርሽ፤

መቼም አላግድሽ።

ሂጂ በይ፤......ደህና ሁኚ፤

የፍቅር አሠሩን እኔም አልመኝ።

# ሔዋን ብቻ ለአዳም

ማን ነበረ ያየው

የዛሬ ሳምንት፣

ነብሱ ከሥጋው ጋር

ስትገጥም ሙግት?

ማን ነበረ ያየው

ከሰውነት ተራ ፍጥረቱ አፈንግጦ

በሐዘን ማገዶ እንደ ቅቤ ቀልጦ?

ማነው ያደመጠው

ምንድናት ሕይወት? ሲል ከንቱ ፍልስፍና

ሰው አላይም ብሎ ዘግቶ በብሕትውና?

ማን ነበረ ያሰበው

ቀድሞ የጠረጠረ፤

የዛሬ ይሆናል ሊልስ የሞከረ?

የተደፋው - አንገቱ.....

የተቆረጠው - አንጀቱ.....

ይመለሳል ያለ ወደ ፊት ብልሀቱ?

ማን ነበር ያየ የሚመሰክር?

የሩቅና የቅርብ ዘመድ ተሰብስቦ

ወዳጅ የተባለ አይዞህ ሲለው ከቦ፣

መፅናናት አቅቶት፣

እንዳልሆነ ሲሆን ያዩ እናት አባቱ

ለሽንቱ ሲወጣ በዐይነ ቁራኛ እንዳልጠበቁቱ

አይደለም ወይ ያ ሰው.....ያ ሐዘንተኛው

ሙዚቃ በጆሮው

ውስኪ በአፉ ያለው?

ውቧን ልጃገረድ የሚያጫፍረው?

የት ደረሰ ጭንቁ!

አልያችሁ.....አትዩኝ ልሙት ልሰቀል

ሚስቴ ከከዳችኝ አልደር አልዋል።

ፈሰሰ ወይ ፍቅሩ

ተረሳ ትዳሩ፤

የካብትሽ ካብቴስ......

በቃ ቁም ነገሩ?

አንዷ የዘጋቻው ልብ ሊከፈት በሌላ
አቤት የሕይወት ግብሯ!
አቤት የሕይወት መላ
ሴት የጣለቻው ሰው
ተራምዳው ያለፈች
ተነሣ እንደ ገና እርም ሊል ባይችል፤
አዲስ ፍቅር ሊሽምት ከሴቶች መሐል፣......
ሔዋን ብቻ እንጂ ለአዳም የነበረች
ለስምንተኛው ሺ ስምንት ሺዋ አለች።

# ባይታይህ ኮከቤ

ተረፍቄ ዛልኩኝ
የገናውን እያሰብኩኝ፤
በሕፃንነቴ የተከልኋትን አበባ
አልቀርም ሳላያት ስባባ፤
ያችን የማርያም መቀነት
ያችን የጨረቃ ድምቀት
እሻታለሁ በሄድኩበት።
እና ባይታይህ ኮከቤ
አትታለል ወዳጄ ልቤ
ብታየኝ ላልተው ሥሮቼ፤

ያለ ቅስሜን ሠውቼ

እጓዛለሁ በርትቼ።

# የተስፋዬ ዛፉ

የተስፋዬ ዛፉ

ሲከረከም ቅርንጫፉ፤

ሥሩ ሲነቃቀል

ሲበጠስ ሲፈነገል፤

ጭላንጭል ስትዳፈን

ብርሀን ዐይኑ ሲከፈን፤

አንጥፌ ደርቤ ማቄን

ዘንግቻት እንቁጣጣሽን

ፀደይ አበባ ዐደዬን፤

በድቅድቁ ተቀመጥሁኝ

ላለማሰብ እያሰብሁኝ፤

የልቤን ልበ - ባሻነት ገሠፅኩኝ

ተስፋ መቁረጥን ተስፋ አረኩኝ።

# ሥጋ ብቻ ለሰው

.....ከንፈረ ፍሕሶ፤ አቤሴሎም ፀጕር፤
ዐይነ ባትሪዬቱ የጥርስሽ ማማር፤
የነፀብራቅ ፈገፍታ፤ የአልማዝ መደብር።
አካሔደ ቆንጆ ስዕላዊ ቅርጽ
እንዲያው አካላትሽ፤ -
ሳያውቁት፤ ሳያውቁሽ፤
የሚያስደነግጽ፤
የተቀኘ አእምሮ ያሰፋል ወበትሽ
አቤት ግሩም አንቺ፣ ምን ይሆን ፍጥረትሽ!
ብዬ የነከርኩኝ -
የወበትሽ አድናቆት በቁሜ ጠምቆኝ፤
እጆችሽን ይዤ ጎርፍ ቢወስደኝ፤
እንዲህ ነው አዱኛ፤
ይህ ነው መንገደኛ፤
ይቃናልን ጉዞው!
ብዬ የፀለይኩኝ፤ -
ዛሬ ለመመለስ መጣሬን አይተሽ፣
ምን አጠፋሁ ስትይ እቱ አይጭነቅሽ፤
በማዕበሉ መሀል ለዕጣሽ ስትውሽ።
ያ ሌላኛው ውበት ተደብቆ ኖሮ፤
ባወቀው አሣፈረኝ።

በቃ ደህና ሁኝ

ከቶ አስታውሸኝ፤

ምድረ በዳ አንጎልሽ፤ ግዑዝ ነው ደንቆሮ!

ሥጋ ብቻ ሠውን፣ አይችል ሊያቆም አሥሮ!

አይችል ሊያቆይ አሥሮ!

# ድንቁርናችንን ይቅር በለው

ወንድምዬ፤

እንደወጣህ ባትመለስ

በዋል ፈሰስ አትከሰስ።

በዋልጌነት አትጠቀስ።

የመንፈስህ ብርታት ንቃቱ

የድምፅህ ውበት ትራቱ፤

ስዕል ነው

ነድፈን እማናኖረው።

......ግን ምነው

እመለሣለሁ ብለህ ሄደኸው

እንደወጣህ ቀረኸው?

ማለት መቼም ልማድ ነው።.....

መንገድ መኖሩን እንጂ

መንገዳችንን ላላወቅነው

ጊዜ መኖሩን እንጂ
ጊዜያችንን ላላየነው፤
አንተ አውቀህልና ወንድምዬ፤
ድንቁርናችንን ይቅር በለው።
ይቅር በውለ።
1963 (ተረፈ ኩራባቸው ባረፈበት ዕለት)

# ውበት ባትከፋ

ደሟ ደም አይደለ፣ የቀለመ ውሀ
ሥጋዋ ሥጋ አይደል፣ የአፈር አምሓ
ጊዜ ናት ወይ ህዋ፣ የሌላት ምጣኔ
እሷ ምንድን ትሆን፣ የሙዚቃ ናት ቅኔ?
እማትመረመር በመለኮት ፋና
ዝም ልበል - ዝም ልበል - እኔ
አላውቅም።
ብቻ ኑረትዋን ልናገር አልፍራ
እንዳሰብ ብርቅታ ድንገት እሚጠራ።
ከሕግ መጻሕፍት፣ ከሀይማኖት መዝገብ
ከብጿን አምባ፣ ከቅዱሳን ክበብ
ሁልጊዜ እማትገኝ፣ ሁሌ እማትነበብ።
ከቃልቾች ድቤ፣ ከጠንቋዮች ኪታብ

ከወያኔ ስብሰባ፣ ከአረሚዎች ምኩራብ
አትባ አትባል፣ የላት ደንብ ገደብ።
በገዳይ ጦር ስለት፣ በካራው እጀታ
በመሠሪ ወጥመድ፣ በሤራ ገበታ
እማትጠፋ ጠፍታ
እማትቀር ሞታ።
መቃጥኑ ባይገድ፣ መረቡ ባይጠፋ
ከእኩያን መንደር፣ ተዘርፋ ተጠልፋ
ለበጎ ብትቆም፣ ለደግ ተሠልፋ
ገነትን ለማግኘት ሰው ሩቅ ባለፋ።

# ቅዠት......ቅዠት

ራስ ምታት ሠፈረበት
ሕልሙና  እውነቱ ተማቱበት
ምኞቱ ከአሚናዊ አድማስ በስተኋላ
ትታየዋለች፤
ታይታው ታሳስበዋለች፤
ከመጥፎ ገደል ተንጠልጥላ።
«ሐሞተ ቢስ፤.....ወኔ ቢስ፤» ራሱን ረገመ
እሷን ብቻ አሁንም አሁንም እያለመ።
የሸሚዙን እጅጌ አጥፎ ወደ ላይ

ለብጣሽ ወረቀት ያካፋል የልቡን ሥቃይ?

ወይስ ድዱን በኮልጌት እያደማ፤

(ጥርሴን አነፃ ብሎ)

ቅንድቡን እየነቀለ፤

(እኳል ብሎ፤)

ፈገግታውን በመስቷት እያስተካከለ

ሌላ ቋንቋ ባይገባት

እንደ ማንም ናትና እንደ ምንም ያባብላት?

ልዩነቱን ይረዳዋል፤

መደዴነቷን ያውቀዋል።

ልቧን ገልጦ ያየ ሲመስለው

ቤህ ነው እሚሣቀቀው።

ተስፋ እሚቆርጠው።

ይሁንና አፍቅሯታል፤........

ተራነቷ ሣይጠፋው፤ ‹ልዩ ናት ሲል አምልኳታል።

ከቀናት እንደሚመረጥ ቀን

ልቡን ዳስሳ ልትበን፤

እንቁጣጣሽ ናት.....ፀደይ፤

ፊተ ክብ......ወይ፤

ዐይናፋር እንደ ጧት ፀሐይ፤

ፈገግታዋን ባንዴ እማታሳይ።

ትመጣለች

እየተከዘች......እየሣቀች፤

(ከሱ በቀር ማንም ባላያት ሁኔታ፤)

ከጥንቱ....

ስታርቀው ከቀድሞ ሕይወቱ።

የተለፈችለትን ቅዠት

በራዕይ እጇ ስታጠልቅለት።

ታዲያ አንዳንዴ እንኳ ሲነቃ

ይሰማዋል፤

ከንቱነቱ.......ምስኪንነት፤

ራሱን እንደ መጥላት፤

እሷንም እንደ መጥላት፤

ግን ሀክ ብሎ ላይተፋት፤

ነብሱ ውስጥ ተሸንቅራ፤

ተቀርቅራ።

ተዳክሞ በቅዠቱ

ተፋዞ በምሬቱ

ራሱን ሴሰለቸው

ዐለሙን ሲጠየፈው፤

መጻሕፍቱን እንኳን ሲያስጠላው፤

(እንዲያ እንደማያፈቅረው፤)

በሩን ዘግቶ ይሄዳል፤.......

በቅምቡራው፤ በብርብራው፤

በጂን፥ በውስኪው፤

ትዝታዋን ሊያሰምጠው

ቅዠቷን በቅዠት ሊያጥበው

# ብቅ በይ ጣይቱ

ብቅ በይ -

ብቅ በይ ጣይቱ፤

ወጣ በይ -

ወጣ በይ ውቢቱ.

ሰላም ሊልሽ ቁሟል ከደጅሽ ፍጥረቱ።

አንገቱን አቅንቶ፤

ያይኖቹን በር ከፍቶ

እጆቹን ዘርግቶ፤

ሆድ - ልቡን አስፍቶ.

አንችው ነው የሚጠብቅ ሳይነጋ ሌሊቱ።

በተስፋ በረታ፣

ድኩሙ ሕዋስ፡ -

የትላንቱን ረሳ፣

በዛሬው ሊካስ

አንች ሆይ! ተገለጭ የልቡ ይድረስ።

ፈርቶ እንዳያበድነው፤ -

የሕላዌ ውርጭ

እንዳይበጣጥሰው፤

የመታከት ቀጭ
በልቡ ያስቀመጠው፤
ስዕልሽን ሞቀው።
ሲያልምሽ ቢያድር ነው፣
አንች - አንችን ማለቱ፣
ብቅ በይ ውቢቱ

# ወጣ በይ ጣይቱ።

አታልቅስ አትበሉኝ
አትሳቅስ በሉኝ
ግዴለም ከልክሉኝ
የፊቴን ፀዳል
አጠልሹት በከሰል፤
የግንባሬን ቆዳ
ስፋት በመደዳ፣
ጨዳራ አስመስሉት።
ግዴለም።
አትጫወት በሉኝ
ዘፈኔን ንጠቁኝ
ግዴለም።

ብቻ፣

አታልቅስ አትበሉኝ

አትጩህ አትበሉኝ።

# “እ ና”

(የሦስት ሚሊዮን ዓመቱ ሽማግሌ)

እና -

የባቢሎን ግንብ ፈረሰና

የብረት ምሰሶው ወደቀና፤

እና -

የቢራቢሮዋ ቀለም ገሠሰና

የጋጋኖው ድምፅ ደከመና፤

እና -

ፀሐይዋም ጠየመችና

ጨረቃዋም ጠለሸችና፤

በቃህ!

የምን እና - የምን ማደናገር

ከእና በፊት ምን ነበር?

# ለራሴ ባላሁት

ገብቼ ሱባዔ

ከብቻ ጉባዔ፤

ላያሌ ዓመታት

በእኔነት ማሳ ተመላልሼበ፤

ወጥቼ ወርጄበት፤

አዝመራ ባጣበት፤

ራሴን በላሁት

እየመነዘርሁት

እያመናዘርሁት።

# በደል

ዝናብ ቢኖር በኛችሁ

ምን ያደርጋል?

አንዲት ጠብታ ሞታችሁ፤

አዝመራችሁን ወፍ አይቀምሰው

የለኝም አቁፋዳ አያውቀው።

እንደ ሌላው አንድ አፍ ሲፈጥርላችሁ

አይደል የበደላችሁ?

ያዘመራችሁንት አንዳትበሉ

የጉሮሮአችሁ ጥበቱ።

ያላችሁን እንዳታድሉ

የእጃችሁ እጥረቱ።

# ሀምሳ እግር

የእሁድ ጧት ፀሐይ

የጀርባዬ ሲሳይ

ስትዳስሰኝ

ደስ.......ደስ እያለኝ

እልም......እልም ሲለኝ፤

አንድ የሚድህ ጭቃ

እግሬ ላይ ወደቃ።

እኔም ተገርሜ መች እንዲህ ላበቃ?

ያልገረመው እሱ

በዚያው ፈሰስ'ሱ

መንገዱን ሲቀልስ

እኔ ማለት ጭስስ።

እኮ እንዴት ቢደፍረኝ?

«ይቅርታ» ሳይለኝ

ብጨፈላልቀው

ከአጠገቤ አልራቀው።

ነካ......ነካ በእንጨት

ገልበጥ አደረኩት

(ትንሽ እንደመቅጣት)

ሊነሳ ሲተናነቅ

እኔ ሣቅ በሣቅ።

..................

ግን የኋላ ኋላ .......ወደ ማታ

ጀንበር ከንፈሯን ስትሰበስብ በለዘብታ

እያሰላሰልሁኝ የጧቱን ሁኔታ

በጣሙን ተከዝኩ

ለዚያ ጭቃ አልቀስኩ።

ሀምሳ እግር እያለው

ቆሞ ለማያውቀው

ድኾ ለሚኖረው።

# ባለ አደራ

የገደል ማሚቶ መጣች

በዘመን ጭራ ታስራ።

የአእላፍ ሙታን ድምፅ

ቋጥራ።

አደራ።

ሕዝብ ፊት ቀርባ ጮኸች፣

አገልግሏን ከፍታ ተማፀነች፣

«ታከተኝ - ተቀበሉኝ፣» አለች።

ግማሾቹ የቻሉትን ወሰዱላት
ያልቻሉትን መለሱላት።
ሌሎቹ ሌላ ነገር አኖሩላት፣
ካንቺ ሌላ - ሌላ አናምን እያሏት።

# እኔና ጨረቃ

እኔና ጨረቃ
ተጓድነን
ልንደምቅበት አደባባዩን
ቀን በቀን
ሸተን፣
እነ ፀሓይን አድንቀን
ባይሆንልን
ጨለማውን እየተመኘን።

# እኮ ልብን እንዴት ያገሰኟል?

እኮ ልብን እንዴት ይገኟል?
ምን ብለውስ ምን ያዋይዋል?
ከየትም መብረቅ አውርዶ
ከሕዋው እሳት - ጉድ አውርዶ

በነበልባሉ ተማግዶ......

ከምንም፥ ጭንቅ ጣርን ዘርፎ

የፍዳ ያለህ ለፍፎ

ስቃይ ደንደ ፍቅር ታቅፎ

በአዶከብሬው ምታት ገዝፎ

በድንገት ውርጅብኝ ተገርፎ፤

ልብ ሲያለቅስ ዐይን ደርቆ

እስትንፋስ ሲወጣ ጉሮሮን ፍቆ

ስር እድነ አውታር ሲነዝር ተጨምቆ፤......

እኮ ልብን እንዴት ይገስጿል?

ምን ብለውስ ምን ያዋይዋል?

የፍዳችን ሌማቱ

የሰቆቃችን ዳሱ

ምንድን ይባል ብልቱ

ምንድን ይባል ሕዋሱ

ምንድን ይባል ያ ኀቡዕ ነፍሱ

የሕይወታችን እኩይ ፍልሱ

የምስኪንነታችን ቅርሱ

የእርግማናችን ትርፍ - ውርሱ

ምንድን ይባል ሕዋሱ?

የበጎነት የፍቅር አበባ

በመንፈስ ተገን አምባ

በቅጽበት ዐይን ስትንጋለል

ስትወድቅ ስትፈነገል፤

ምንስ ቢሉ ምን ይረዷል?

በእኩለ ቀን - ቀን ሲጨልም

ያይንን ብርሃን ልብ ሲያጠይም

ሙሉ አካልን ሲያፍገመግም፤........

ሣቅ - የሩቅ ሀገር እንግዳ

የመንፈስ የጥርስ ባዳ

አልደፍር ሲል አልደፈር

ሲሸሽ የክናፍርን ድንበር

ድምፁ ሲማስን ባሻገር፤......

ልብን ልበ ባሽነት ሲጫነው

ማስትዋል ሀብቱ ሲሳነው

ውጥር ቅሬታ ሲያፍነው

ለራሱ ይቅርታን ሲነፍገው፤.......

የጉድ አሻሮ እየቆላ

ሲጠምቅ ሲጠጣ መርዝ ጠላ

የቁም ተዝካሩን ሲበላ፤.....

እኮ ልብን እንዴት ይገስጿል?

ምን ብለውስ ምን ያዋይዋል?

# አጸለሌ

የፀጥታ ጩኸት፣ የሞቱ ሕያውነት
የትላንት ዛሬነቱ፣
ከርሞ ማሙዬነት፣
ዘወትር ልጅነት።
ሲሆኑት ማድከሙ፣ ሲያመልጡት ማማሩ
ትዝታው መጣሙ፤ ቅርበቱ ማቃሩ።
ቀርቷል ቀርቷል ሲባል፣ ፈጀ ገደል ገባ
ዛሬም በቃሬዛ፣ መተኛት ባንቀልባ።
ባትጠፉኝ ነው እናንተ፣ የሽማግሌ ሕፃኖች
በጥንቱ ሕልማችሁ ዛሬውን አባባዮች
መፈንደቅ መፈንደቅ
መፈንደቅ መፈንደቅ፣ በዚያ ቀን ግርሻታ
ሳይሆን......መግፋት መግፋት ጧትን ወደ ማታ።
ድካም እንጂ ትርፉ፣ መች ተገለለና
ትላንት ከዛሬ ከዘንድሮስ አምና ፡
ስንቴ ተጫውተናል
ስንቴ ተጫውተና፣ ዛሬስ አጸለሌ
በጉርምስና አምባ፣ በስተርጅና ቆሌ።
አጥሩ ሲዋቀር - ሲማገር - ሲታሰር
ሲደለቅ - ሲጨረቅ - ሲጠብቅ - ሲጨፈቅ
ማጮለቅ - ማጮለቅ - ማጮለቅ - ማጮለቅ።

አየሁ ጓጓሁ ብሎ

ከሩቅ አስተውሎ

ይዝረበረብ ምራቅ፣ ከልብ ምላስ

ከእያንዳንዷ ሕዋስ

ወላሏን ለመርገጥ ግቧ ለመድርሥ።

«አጸለሌ

የብር መስቀሌ

ተው አስገቡኝ ዛሬ»

ያሜካላ - እድሞው ያሜካላ

የሚናውዝበት የነብር ቡችላ፤

ደሞ ቃፊሮኡ .....እኒያ ግንዲሎቹ

እኒያ ችፍርጎቹ፤ እኒያ ምስማሮቹ

ግርማው......ግርማው የዓይናቸው

ስብእናን ሽምቃቂ፣ ደም - ተስፋን አናቂ።

ክብደቱ.....ክብደቱ የፈታው

የፊት ወዝ አባናኝ፣ ትህትና አባካኝ።

ሲማልግ.......ሲማልግ ድምጻቸው

ሰው መሆንን ገዳይ፣ በጎነትን አቁሻይ።

«አ.....ጾ........ለ.......ሌ

በርር መስቀሌ

አ.....ና.....ስ.....ገ......ባ.....ም ዛ......ሬ»

ያ የልብ ምላስ፤ ያ የቅንጣት ሕዋስ

የተሰጣት ቁርበት፤ ውሀ - አልባ ንፋስ

ያደናቀፉት ትል፣ ወይ አባጨጓሬ
አይወጣም ዳግመኛ፣ አምሓዬን ብሎ
ወይ ፀደዩን ብሎ፣ ወይ ጨረቃን ብሎ
ወይ ራሱ አምኖ፣ ወይ እግዜሩን አምኖ
ይጠይም ይሞታል፣ አንባው ጢስ ታፍኖ።
ዘንዶ ተጠምጣሚ! እባብ ተወርዋሪ!
እና?
እናማ የከሸፈን ዕድል አለባብሶ ቀብሮ
ለጊዜው ጊዜውን፣ በአሜን አሳድሮ
ልጅነትን መኖር፣ ዳግመኛም አምርሮ።
መጠጣት ዝቃጩን፣ ወይ አጥልሎ አቅርሮ
በቀን ሕልመ ጣባ፣ ጠልቆ አንቆርቁሮ።
አለዚያም መጫወት......መጫወት ላንዳፍታ
ማባበል ማባበል፣ የሕይወትን ድንፋታ
በርከክ በርከክ ብሎ
ጭንቀትን አታሎ፤ -
«ጉልበቴ በርታ በርታ
አበላህለሁ የሽምብራ ቂጣ
አሁንም አይደል ወደ ማታ
.......ወደማ......ወደማታ.......
(ወደማታ......ወደማታ......ወደማታ
የቀትር ላይን ጨዋታ፤
ያጸለሌ ጨዋታ፤

ያጸለሴን ሕይወት አለኝታ - ቅሬታ።)

# ተይ አይሆንም ነብሴ

የቱ ይሆን ኩነኔው፣ የትኛው ነው ፅድቁ?
የምድሩ የቅርብ የሰማዩ የሩቁ?
በእንጀራ በጠላ በሥጋ ሢሣይ፤
አካል ብቻ እንጂ፣ ነብስ አታድግም ወይ?
ነብስ እንደነበልባል፣ ሥጋ እንደ እንጨት፣
አይደል ባንድ ዕጣቸው፣ መዳፈን መብራት?
መክሰል ወደ መፍካት?
የት ነው የሥጋ ደብሩ፣ ደሞ የነብስ ቤት?
መቼ ነው ለየብቻ የተካለሉት፣ ጎጆስ የወጡት?
ልሂድ - ልሂድ አለች፣ ወደ ሕልሟ ኬላ፣
ሥጋ ሐር ልብሷን ነብሴ አውልቃ ጥላ፣
ከፅድቁ ገበታ፣ አብርሃም ልትበላ።
ተይ አይሆንም ነብሴ፣ ሥጋሽ ይታሠብሽ
ተመከሪ ነብሴ ምድሩም ይታወስሽ
አልፋ ወ ዖሜጋ ጭቃው ነው ገነትሽ።
የዘላለም ቤትሽ።

# ለራስ የተጻፈ ደብዳቤ

ጋሼ፤

እንደምን ሰንብተሃል?

ሥራውስ እንዴት ይዞሀል፤ ተስማምቶሀል?

እስቲ በርታ፣ ያባባም ፀሎት ይሁንህ

ሰላሙን አይንፈግህ።

ጋሼ፤

ዛሬ ይህን ወረቀት ስጽፍልህ ታግዬ

እንዳይመስልህ የተፋታሁ ከአያሌ ወራት ዝምታዬ

በእግዜሬ፣ በወገኔና በራሴ፣ ካወጅኩት ኩርፊያዬ

ካደበተኝ ሥቃዬ፣ ካነዘበኝ ምንዳቤዬ፣......

እንዳይመስልህ ያመለጥኩኝ፣ ከብቸኝነት ግዞት ዋሻዬ።

አሁንማ መች ዝምታ ብቻ

አሁንማ መች ኩርፊያ ብቻ

አሁንማ መች ብቸኝነት ብቻ

ፍርሃትም አሳጥቶኛል፣ እምቆምበት ዳርቻ፣

እምገባበት ሥርቻ።

አንድ ወንድሜን አንተን፣ ጠልቼ አይደል አለ እምጻፌ

ምን ሊበጅህ ብዬ እንጂደህና ነኝ ብልህ ባፌ።

አሁን ግን ፍርሃቴ ነው፣ ይህን ደብዳቤ የላከው

በዚህ መካነ ደይን ተቀብሬ እንዳልቀረው

የዚህን ምድረ - ፋይድ ታሪክ ሳላወጋ ሳልናገረው።

ይልቁንም ያይኔን እወነት፣ ለልቤ ያጫወትኩ ቢመስለኝ

ለራሴ የጻፍኩትን ደብዳቤ፣ ላንተ መላኩ አሰኘኝ።

ጋሼ፤

ከንድ ዓመት በፊት፣ ግብር ለመሰብሰብ ተቀጥሬ

ወደ ዚኅ ገጠር ስመጣ ስንቄን - ጓዜን ቋጥሬ

ይህን ተአምር መች አስቤ፣ ይህንን ጉድ መች ጠርጥሬ?

አየህ ተዚያ ተከተማ ተቀምጠህ፤ ገጠር ሲባል ተቃሉ

ትቅርጽ ይሆናል የልምላሜን ጣዖት በውሉ

የወንዝ አረንጓዴውን የሣር ቅጠሉን ሁሉ።

በቅሬ - በሰንበቴ - በዕቁብ፣ የነዋሪውን ተቃቅፎ

በወንፈል - በማኅበር - በሠርግ፣ ባንድ መቆም ተደጋግፎ

የሐሴትን መና ተፋትቶ፣ የፍቅርን ጽዋ ተዛርፎ

ያሳይህ ይሆናል፣ የከተሜ ሕልምህ አግዝፎ።........

አዎን፣ ያሣይህ ይሆናል የከተሜ ሕልም ምናልባት

ፏፏቴው ሲያሽቆለቁል፣ ከዐለት አናት

ጪስ ሲፈትል፣ ሲያገምግም እንደ መዓት

እመር ብሎ፣ ዘለቅ ብሎ፣ ቋጥኝ ሲያርም ሲፈነግል እንደ ጠላት

ይታይህ ይሆናል - ልቆ በኪነ ፍጥረቱ።

በአረንጓዴው መስክ ላይ እምቦሳዎች ሲፈነጩ

አእዋፍ - የዱር ጣፋጭ ልሣን - በየዛፉ አናት ሲያፋጭ

የእረኛ ዋሽንት ሁሁታ፣ በየጎራው ትንቢት ሲያወራ

ያራዊት ግሣት ግምግምታ፣ በገመገሙ ሲደራ፤

መኸሩ ሲዘናፈል፣ እጅ ሲነሣ በንፋሱ

ዕፅዋት ሲምነሸነሹ፣ ቁንጮአቸውን ሲነሳነሱ፤.......

ይታሰብህ ይሆናል፣ ገጠር ሲባል መንፈሱ።

የምሽት ጀምበር ስታቅማማ፣ እምራብ ቤቷ ልትገባ

ምድር ሲዳዳት ከል ጨርቋን፣ ስባ ልትወስድ ከጊዜ አምባ

አባቶች በየጉብታው ዘና ብለው ለምለም ሳር ላይ

በእደ ጎሊናቸው ዳሰው፣ ያባቶቻቸውን ትውፊት - ሙዳይ

ሲያወርሱ ለልጆቻቸው፣ የስብእናን ቋሚ ምስናይ

ብል አይበሌን ቁም ንዋይ

የብሔር ክብር ምስካይ

ምስጥ አይበሌን ቁም ሲሳይ፤.......

ታይ ይሆናል፣ የከተሜ ዕራይ ሕልም መሣይ።

የሕይወት ልብ በአውድማው፣ በጓጥ በስርጓጉጡ

በአረሁ ላይ በገደሉ፣ በፋልማው ላይ በዘብጡ

ለቅጽበት ሳይሰናከል ሲንር ሲመታ በቅጡ

ያሰማህ ይሆናል፣ የከተሜ ሕልምህ ቅንጡ

ግን ላንዳፍታ ነቅተህ፣ ወርደህ ከከተሜ ሕልም ዙፋንህ

ፍቀድልኝ ወንድምዬ፣ እዚህ ምን እንዳለ እኔ ልንገርህ

ዐለት ስር ሰዶ

ዐለት ወልዶ

እዚህ ዐለት

እዚያ ዐለት

የኮረብታው አናት - ዐለት

ዐለት

የላይ የታቹ መሠረት።

ቢያዩ ድንጋይ

ቢያሹቱ ድንጋይ

ጎንበስ ቢሉ ድንጋይ

ቀና ቢሉ ድንጋይ

ቀና ቢሉ ድንጋይ

ዋዕይ የሚያዘንብ ሰማይ።

ወንዞች ኩሬዎች

የውሀ ጥም እስረኞች

የሰው ያዕዋፍ በድን ታቅፈው

ያራዊት መቃብር ሆነው

ተኝተዋል፤ ዐለት - ጎድናቸውን አግጠው።

አፈር የሕይወት አልፋ

አፈር የሕይወት ሀሌታ

አፈር የልምላሜ ኪነት እፍታ

ተቋቱ ላይ ተሟጠጠ።

አፈጀ አበቃ አጠጠ።

ሥጋ ነበር አፈር ‹ሚሆን

በቁሙ አጥንት ያጣጣመው ጎን

ዐለት ሁኖ ወደ ዐለት ተመለሰ፤

ኮረት ሆኖ ፈሰሰ።

ጠጠር ሁኖ ፈሰሰ።

ጠጠር ሁኖ ተዳረሰ።

አልተርፍ አለ ሰው ለአሞራ
አልተርፍ አለ ለጥንብ አንሣ ለጆቢራ
ከላዩ፣ መቅሰፍት ቸነፈር እያጓራ
ከሥሩ፣ የድኝ እቶን እየደራ
ውስጡ ውጪው ተረምጦ በመከራ
ጽላሎት ሥጋው፣ ጽላሎት ነብሱን አቅራ፣
ወገሸ ሰው ከሰውነት ተራ።
እንደው ብቻ በጽድቁ ታዛቢነት እንደ ታፈነ
እንደ ተከነ፤ - እንደ ባከነ - እንደ ተነነ፤
ጥርኝ አፈር ያርገኝ ምኞት ሆነ።
ጋሼ፤

ሰው ከልማዱ ተነቀለ፣ ከባሕሉ ተራቆተ
መኖር ምን እንደሆነ ሳተ፤
በገዛ ታሪኩ ተረተ።
ከጓዳ - ከአውድማ አንዲት ጥሬ ብትጠፋ
የፍቅር ድምፁ ከፋ።
የእምነት ሚዛኑ ተደፋ።
ባል ለሚስቱ፣ ክንዱን አላንተርስ አለ
አባት ልጁን፣ በፍርሃት አስተዋለ።
ጋሼ፤

በሉካንዳ አራጅ ዐይን፣ ዘመድ ዘመዱን ሲመለከት
ሰው አውሬ ነው ማለት
ምንኛ አሰቃቂ እውነት!

ልብን እሚፋጭር ስለት።

ምንኛ አስቀያሚ እውነት!

እሚለበልብ ቃር - ግለት።

ኧረ እግዚኦ! ቤህ ምድረ - ፋይዳ ምን ሰው ቀረ

ተፈጥሮው ያልገሠሠ፤ ሰብዓዊነቱ ያልሻሸረ

አሻራው ያልሟለጠ፣ እንጥፍጣፊው ያላጠጠ

የሁነት እርሾው ያላረጠ።.......

ችጋር ብቻ እንጂ ቀጠና

ደዌ ብቻ እንጂ ፈተና

ግዙፍ ነስቶ፣ ነብስ ዘርቶ እሚፋጭ

ከአእላፍ ኤኬራ እሚጋጭ።

ሌላማ ምን ሰው ቀርቶ፣ ሌላማ ምን ፍጡር ተገኝቶ

ነበር መልኩን አቆይቶ፣ ቀለሙን የያዘ አካቶ

ተምፀት አምድ ያላኖረ፣ ያበከሮ ስሙን ፀንቶ በቅቶ

ኧረ ምን ፍጡር ቀርቶ፣ ኧረ ምን ሰው ተገኝቶ?፤

የዚህ ሁሉ ጎግ እድል፣ አንድም ብዙም ሁና ተሠብራ

ማንም ማንን አይጠራ።

ቀድሞ ለራሱ ማን ሆነና፣ ማን ለማን እጁን ሊዘረጋ

የማንን ጦርነት ማን ሊዋጋ?

ባንድ ተሰድሮ ሲያምም ሲታመስና ሲጠበስ

ማነው ለማን ሞት እሚያለቅስ?

አንበሳ ምንድነውና ምንድነውናስ ለቅሶ?

ከእንጉርጉሮ ባለፈ እንጉርጉር፣ የስሜት ዘሃው ተበጥሶ

ህሊና፣ ከዘለለት ልማዱ ተፋልሶ፣ በራስ ቁስል ጉም ተላብሶ
እንባስ ምንድነውና ምንድነውናስ ለቅሶ?
ጋሼ፤
ኧረ ምንኛ ተአምር አለ፣
ተፈጥሮ ቀደም ባሕሏን፣ እንደግትቻ ወዲያ ጥላ
በሞትና በሕይወት መሐል፣ የትንግርት መንደር ከልላ
‹ያልኖረ› ወይ ‹ያልሞተ› እሚሰኝ ፍጡር አከታ
ስታደድበን ስታሞኘን፣ ለደረቅ ዐይናችን ጋርዳ ዘግታ።
ተፈጥሮ የጊዜ ንፋስ፣ ከጭብጣችን ዕንቁ ስትቀማ
ኩራዛችንን ስታጠፉ፣ ስትጥለን በጸለማ
አይለየን አንዳንዴ ግብሯ
አይታወቀን አልፎ አልፎ ስሟ።
ቀንቋምኮ ዲዳ ነው፣ ገጿን መለየት የተነሣው
እንድቆቅልሿን መፍታት ያቃተው ድምጿን ማወቅ የገደደው።
እስፔክትረም - ብረሃን ርችት - ቀስተ ደመና
ሲነጣጠል በቀለማት ሲበታተን እንደፋና
ማን አወቀው - ማን ለየው፣ የዛን የፅልመት ገበና?
እናም ቋንቋም፣ የሥልጣኔ ቁራኛ፣ የሥልጣኔ ተጓዳኝ
የስሜትን እውነት ገዳይ ነው፣ ያይንን ገሀድ እውነት አፋኝ።
ጋሼ፤
እነኢስ አዘንኩ ለዚህ አምባ፣ እኔስ አዘንኩ ለዚህ ዘመን
ለእሚፎክት ለሚያቃስት በመፃጉአን ደረመን
ለሚሰቃይ ለሚታመም በአእላፍ ደዌ - ሰቀቀን፤

እኔስ አዘንኩ ለዚህ አምባ፣ እኔስ አዘንኩ ለዚህ ዘመን።
ሕፃናት መንቆር፣ ማጉርጥ ባወጡበት
አጥንት በተገተጉበት
በድን - በላ በሆኑበት እርመ - በላ በተባሉበት
እኔስ አዘንኩ ለዚህ ዘመን።
እናቶች ሰብእናቸውን በጠረጠሩበት
እንደ ትኋን እንደ ቅማል ዕጭ በፈለፈሉበት
የእንግዴ ልጅ፣ እንደ ሕፃን በታቀፉበት
የራሔልን እናባ በዋጡበት
እኔስ አዘንኩ ለዚህ ዘመን።
አባቶች በነጭ ጠጉራቸው ባፈሩበት
አድባራቸውን በረገሙበት
ሕልማቸውን በተሳቀቁበት
ያበሻ ማቅ - ቱቢት በተፈተለበት
ነጭ ማተብ በተገመደበት
እኔስ አዘንኩ ለዚህ አምባ እኔስ አዘንኩ ለዚህ ዘመን።
የታሪክ ደረባ ሲከፈት፣ ሲከፈት የታሪክ መዝገብ ብራና
መቼም ሳያኖረው አይቀርና፣ ሳይከተብው አይዘነጋውና
ምንድን ነው ይጥራው፣ ይህን ዘመነ መንሱት፣ ይህን ዘመነ - ፈተና?
ይበቅል ይሆን ከዚህ ጠፍ ላይ፣ ከዚህ መና ከዚህ ወና
ተስፋ ማድረግ እሚያቅ ኅልው፣ ሣቅ እሚያቅ ሰብእና
የሰላም ሪቅ የጤና፣ የፍቅር የአንድነት ጋዘና.....
ይበቅል ይሆን?

በትንሣኤ እንደናምን፣ ያሸት ይሆን አዝመራው?
ያፈሩ ይሆን ተክሎቹ? ያብቡ ይሆን ዕፅዋቱ?
ይተሙ ይሆን ንቦቹ? ይዘምሩ ይሆን ወፎቹ?.......
በትንሣኤ እንድናምን!
ይደራ ይሆን ኮከጽባህ፣ የእንቁጣጣሽ ችቦ
በእምነት በአለኝታ ጉንጉን ተውቦ፣ በቀስተ ደመና ተከቦ
ተሞሽሮ በዐደይ ወርቀ ዘቦ፤........

ይደራ ይሆን?

ይኖር ይሆን ወይ አርማ፤ ይኖር ይሆን ወይ ባንዲራ፤
ሰውን የመሰለ ቀለም ያለው፣ ሰውን የመሰለ አሻራ፤
እማይወድቅ እማይታጠፍ ሰንደቅ እማይሰም፣ እማይዳፈን ደመራ?......

ይኖር ይሆን?

ጋሼ፤

የከተሜ ሕልምህ ከፊትህ ካልተጨፈቀ እንደ ጅብራ
ይታይህ ወንድምዬ የዚህ ሕዝብ አሣር እምከራ።
ምንም እንኳ የምፀት ቢሆን፣ የናንተና የሱ መታደም አብሮ
ምንም እንኳ አንድነታችሁ፣ ቢሆን የአባብ የጓጉንቸር ኑሮ
‹መሠልጠን› ‹መሠይጠን› ሳይሆን ዐይናችሁ ይከፈት ዘንድሮ።
ለናንተ ማዳበሪያ ሁኖ ከወንዙ አልፎ ራሱን የገበረ
አንደበቱ እንደበሬው በዝማም ታስሮ የኖረ
የዋህ ፍጡር - ጉልጥምቱ ነው እዚህ የቀረ
አሰር - ፍቅፋቂው ነው እዚህ ያደረ።
በሞቱ እንደዋኛችሁ በንጥፈቱ እንደፋፋችሁ

በዋይታው እንደሣቃችሁ

በጣመኑ እንዳሣረፋችሁ፤........

በፃዕረ ሞት ጣቱ ሣይጓጉጣችሁ

በዐለት ጥርሱ ሳይቦጭቃችሁ

እስቲ በሉ ምንድን አለ በጃችሁ በተራችሁ?

እስቲ በሉ፣ ለጥያቄው ምንድነው መልሳችሁ?

አወን፣ ዛሬም ከከተማችሁ፣ የሙታን ገዥ፣ ፈላጭ ቆራጭ አሳሪ

የሞተውን አሚች፣ የተቀበረውን ቀባሪ

የአከሬንና ግብር አስገባሪ፣ የሙታን ላብ አቅራሪ

ስትልኩ ላይ፣ የእብድ ሣቅ ያስቀኛል

መሠሪ ወጋችሁን ማወቄ ጠልቆ ይወጋኛል።

ግና ድሮም እንጂ፣ በአንበሣ መንጋጋችሁ በነበር ማጉርጣችሁ

በጥንብ አንሣ መንቆራችሁ በላሸ በእባብ ምላሳችሁ

በጊንጥ በዘንዶ ጅራታችሁ፣ በገበሎ ትንፋሻችሁ፤........

በሌላማ ማን ሊያውቃችሁ? ማን ሊያውቃችሁ?

ከቶ እዚህ፣ ማን ምን አለው ከናንት ወሬ አሉባልታ

እናንት ዝባዝንኬ ቀረርቶ፣ ከናንት ሽለላ ድንፋታ

ከናንተ ጂኒ ቁልቋል ከናንተ ተረብ እሩምታ?

አወን እንደተረታችሁ፣ የደላው ሙቅ ያኘካል

ሕይወትን በመታደግ ሳይሆን በጥናቷ ብቻ ይረታል።

እና እዚያው እርስ በርሳችሁ ብትመሣጠሩ፤

ዕፁብ ድንቅ ተዓምር ብትለፍፉ

ተረታተረታችሁን ብትወጉ በኔነት ማራቶን ብትዳፉ

በቋንቋ ስለት ብትዋጉ፤ ለክብር ለስም፤ ብትዳሙ ብትጋፉ

ለአለሁ ባይነት ብትፏድዱ ብትጣፉ፤......

በዚህ ሙት ሕዝብ በድከሙቱ ብትልቁ፣ በፈተናው ብትበልጡ

በሱ ውድቀት እናንተ እርካብ ብትረግጡ

በብሶቱ ብትፈይዱ

በመከሊቱ ብትነግዱ፤.......

ይህ ፍፁም ባድማ፣ ይህ ፍፁም ድቅድቅ ጨለማ

እሚበራ እንዳይመስላችሁ በናንተ የይስሙላ ቁራጭ ሻማ።

ግን መጋረጃው ያልተነሣ ተውኔት

ያልተፈታ እንቆቅልሽ አለውና ጨለማ

ነፋስ - እሳት ገሞራ ሊታቀፍ ይችላልና ጠፍ ባድማ

ዐይን ያለው ይይ!

ልብ ያለው ያስተውል!

ጆሮ ያለው ይስማ!

ጋሼ፤

ምናልባት ፊትህ ቅጭም ቢል፣ ቤህ ደብዳቤዬ

የእውነት ምሬት ነው ዋቢዬ።

እና በል ደህና ሁን፤ ይህን ደብዳቤም አኑርልኝ

እናንተ ጋ ላለው እኔነቴም - ነውና የተጻፈልኝ።

# እኔ ሆይ ተጠየቅ

እኔ ሆይ ተጠየቅ፤ -
ለስንት ዛሬ ሙሾ አዋእረክ
በትላንት ቀሣህ እንደነበርክ
የቀንህ ቁመና
ሲልቅህ እንደምሽት ጥላ?
ተጠየቅ እኔ ሆይ፤ -
በምዕተ ዓመት ክፋይ ክፋይ
ስንት ደቂቃ ስንት ሰኮንድ
አልነበርክም ብሎ ይፍረድ?

# ሰብአ ትካት

ያባት መቃብር አንጣሎ
በገበናው ተጠልሎ
ዓፅም ያለምልም ብሎ
ኂ ብሎ መተኛት
በቀን ማንቀላፋት።
ያያት የቅድመአያትን ሕልም ማመንዥግ
መጠቅጠቅ የነበርን ወግ መሰግሰግ።

የሣባ ዘመን ቁስል ብካይ
ላይሽር በቴዎድሮስ ክብረ - ሰማይ
መስለምለም.......መፍገምገም......መከርተስ.......መላም
ፀዳል ......አልቦ መጋም።
ምን ዐይነት አድነበት?
ሰዋሰው ሲሰወሰው ቃላት ያፈጁበት
ልማማቸውን ያደሩበት።
የዘመናት ትንፋግ - ከረጢት
ፋደት!
የእጅ እግር ሠነሠለት
መተት!
ምን ዓይነት አንደበት?......
ኖርን ያላችሁ ሳትወዱ
ሥር ምሳችሁ ሥር ሳትሰዱ
ያመት ዓለም ሰዎች ዕድሜ - በላ
ተቀጥላ።
በሺ ዘመን እግሮች መውተርተር
በከርሞ ጥጃነት መግተርተር
በልማድ - ልምድ መወጠር
በእምነት - እምነት መጠበብ
በይሉኝታ - ይሉኝታ መታለብ።.....
የኛችሁ እነሱአችሁ ተሻኩቶ
ድርና ማግ ሁኖ ተስማምቶ

የተቃርኖ ውብ በረከት ሐራም ሁኖ
የመፋጬት አምሓ - እሳት በኖ ተኖ
ዓይን ያላቸው ያስተዋሉ ሲጋዙ
መናፍቃን ሰማዕታት ሲወገዙ
ቀለለ፤ - የመጠራጠር ቁም ነገር ደርዙ።
ጨለመ - የጥበብ ሻማ ኩራዙ።
በበለው በለው!
በአምታታው በአዋቃው!
በሙቶ ዓይነት ጥለፈው
በሺ ዓይነት መትተው
ልንቃ ሲል
አንገቱን ሲል።
በቀልቡን ንሣው
በአሣሥቀህ አስለቅሰው
በዓይነ ቁራኛ ጠብቀው
ቀና ቢል ራሱን ቀጭ
አቤት ቢልህ፣ ቢማፀንህ
ጭጭ......ምጭጭ......እርር።
ለልማት ሳይሆን ለጥፋት
ጸሎት - ምህላ - ትጋት
ካንድ ረግቶ ጥንጣን ማድራት።......
የገደል ማሚቶ አንቀላፍታ፣ ድምፃችሁን ተንተርሣ
በእሣት ዳር ምን ይወሳ?

መጓዝ ሆነ በዳበሣ.......በደምሣሣ......በአሰላ
መልካችሁ አይቀረጽ፤ አይጠፋ......እየከሣ.....
እየሣሣ።
ቀርቶ ተደቡኖ፣ በእረኝነት ገሣ።
አይ እናንተ ያባቶቻችሁ ልጆች!
ያያቶቻችሁ ወላጆች
የዘመን አርማችሁ
ልዩ ነበር ባንዲራችሁ
የተነደፈበት የየዋህ ፅድቃችሁ።

# ከአክሱም ጫፍ አቁማዳ

ትግራይ ላከ ወሎጋ አበድረኝ ብሎ አንድ ቁና ጤፍ
ወሎም አፈረና የለኝም ማለቱን ባህሉን መዝለፍ
ቆሌውን መንቀፍ
ላከ ወደ ሸዋ ምናልባት ቢጠሰው ለሰው እሚተርፍ።
ሸዋም አፈረና የለኝም ማለቱን ወደ ሐረር ዞረ
ሐረርም መልሶ ባሌን አተኮረ
ባሌም ወደ አርሲ አርሲ ሲዳሞን
ሲዳሞም ተክዞ፣ ግን የለንም ብልስ ማን ያምነኛል ብሎ
ወደ ጋሞ ላከ አቁማዳ ጠቅሎ።

ጋሞን ብርድ መታው ሐዘን ገባውና
የራሱን ምንዳቤ የግል ስቅየቱን ችሎት በጥሞና
በጋቢ ደቡኖ የልቡ ጠባሳ ሲኖር እንደደህና
ዛሬ የወንድሙን የእርዳኝ አቤቱታ መስማት አልቻለና።
አወጥቶና አውርዶ ላከ ወደ ከፋ እጅግ አስተዛዝኖ
ከሀፍረት ያድነኛል፤ ከረሀብ ያወጣኛል ሲል ባያሌው አምኖ።
ከፋ እንደደረሰው በድንገት አቁማዳው በነብሱ ዋይታ
ሐራራው ተሰማው የሥጋው ድንፋታ
በብልሀት አዛጋ ቆይቶ ቆይቶ የተሰፋ ጠል ቀዳ
ሲልክ ከኢሉባቦር አበድረኝ ብሎ እህል በአቁማዳ።
ጭምቱ ኢሉባቦር ይኖር የነበረ የቤቱን ጉድ ጓድ
　　በሞኛሞኝ ገላው ቆዳው ውስጥ ወሽቆ
ጠየቀ ወለጋን ሐፍረቱን ደብቆ ኩራቱን ዘቅዝቆ።
ኬት አመታ ብሎ ወደኔ ላከብኝ እያለ ወለጋ እጅጉን ተደሞ
ሄደ ወደ ጎጃም ዛሬን ሁነኝ ብሎ ሊማፀነው ቁሞ።
ጎጃምም ተሰምቶት፤ ሰቀቀን ሐዘኑ፤
　　ደረት እየመታ፤ ቅኔ እያወረደ እንባ እያፈሰሰ
ወግና ኩራቱን በየቦዳው መሀል እየነሰነሰ
　　ዐባይን ተሻግሮ ከጎንደር ደረሰ።
ፋሲል ላይ ተነጥፎ፣ ጎንደርም ሐዘን ላይ ነበረ ተቀምጦ
ተድላ ልጁ ሙቶ፤ ገናን ክንዱ ታጥፎ፤ በዘመን ተድጦ
ጎጃም መጣ ሲሉት የእዝን የተመኘን ልቡን በታዘበ
　　የኩራት ካባውን ሊጥል አንጓበበ

የወንድሙ መምጣት፤ እቅጩ መንስዔ መሆኑን ሲረዳ ረሀብ አበሳ

ጥንትም አልሆነኝም ከእንግዲህ ይበቃኛል ለይሉኝታ አልሳሳ

ብሎ ከኤርትራ እህል ለመበደር በርትቶ ተነሳ።

የዘመዱ እጦት ነበርና እጦቱ በዝቶ ሰቀቀኑ

ኤርትራ ታመመ ደም ጎረፈ ከዓይኑ

ወደ ኤርትራይ ላከ መላ ባገኝ ብሎ ከአደራ ደብዳቤ

«እባክህ ላክልኝ አንድ አቁማዳ እህል ልሞት ነው ተርቤ።»

ትግራይ አስተውሎ አቁማዳው የራስ መሆኑን ለይቶ

ሐዘኑ አነቀው፤ ትንፋሹ መረረው ትካዝ ሆዱ ገብቶ።

«እኔና ወንድሞቼ» አለ በለዘብታ

ለራሱ እንዲወራ የራሱን ስሞታ፤

«እኔና ወንድሞቼ ሁላችን......ሁላችን

ከባዶ አቁማዳ ነው እሚዛቅ ፍቅራችን

ይህ ነው አንድነታችን

ይህ ነው ባህላችን

ዘመን ማዛጋቱ በያንደበታችን።

ለኋላ ትውልዶች ተረት እንዳይመስል ይህ ብካይ እሮሮ

ይህ ጠፍ ስብእና ይህ ስቁይ አእምሮ

እንዳኖረው ያሻኛል ይህንን አቁማዳ ከፍ ካለ ሥፍራ

መጥቶ እንደባንዲራ

ምንም ባዶ ቢሆን በውስጡ አይጠፋና የታሪክ አዝመራ።»

ይህንን ተናግሮ ከአክሱም ሐውልት ዘንድ ትግራይ ተጠግቶ

አንዴ እየፀለየ አንዴ እያአወእመረ ያለ መጠን ተግቶ

ጫፉ ላይ ሰቀለው ያን አቁማዳ አወጥቶ።

እንኳን በቃኝ

ይኸ ከንቱ መባባል፣ ይኸ ከንቱ መሸናገል

ይኸ ከንቱ.....ከንቱ መዳለል

ላናልፋት ያችን ዕውነት - ዐቀበት

ያችን የመፈተኛችንን እቶን - ዕለት

በቃኝ.....እኔስ በቃኝ።

ባንደበታችን ወለላ፣ ጭራቅ ከሆነ እምናፋፋ

ቀን አግዞት ሲጠነክር፣ መርዝ ተፍቶ እሚያስተፋ

ለእሚያዋጋ ለእሚያስቃስት፣ ለሚያጣጥል ለእሚያዳፋ

በቃኝ......እኔስ በቃኝ።

ሰንበሌጡን እንደ ብረት ዘንግ

ልግጫውን እንደ ቋሚ ወግ

ወስደን፤.....ፍቅር አልነው

ያለ ግብሩ ክነነው ያለስሙ ሰይመነው

ታድያ ዛሬ

እውነት ቁርሾ አለኝ ቢል፣ ቢፋጠጠን እንደ ጠበቃ

ቢሣለቅብን፣ ቢያፌዝብን ቢታበይብን ቢመሰቃ

እውነት አለውና እወንት

እሚፋጭር እንደ ካራ ስለት

እሚያሰማን እንደ ብረት ግለት፣

በቃኝ.......እንኳን በቃኝ።

እነሆኝ ወስጃለሁ፣ ውዳሴዬን - እርግማኔን

ያው መልሻለሁ የቃላት ንዋዬን - ኪሳራዬን
ዳግመኛ በጉም ጭጋግ፣ በደመና በጀገጀግ
ላንኳኳል ልንሣሣል፣ ላንተያይ በቅጥ በወግ
በቃኝ......እኔስ በቃኝ።
እንኳን በቃኝ።

# ጥናቱን ይስጥሽ እማማ

አየሽ.......
እንዲህ እንደዛሬው ፍቅርሽ ይቀነቅናል
የጠረጉለት መንገድ እንኳ ያነቅፋል፤
እንዲህ እንደዛሬው ፍቅርሽ አልባበል ይላል
ሲማጠኑት እንኳ ይጨክናል።
አትታዘቢውና መታዘቤን
አልሁንብሽና ተገዳሪ
እርመ - በላ ሁነሽ ታየሽኝ
ልጅሽን እንኳን የማትምሪ
እጦትሽን የማትመሽኚ
ጉድለትሽን የማትቆጥሪ
እንፉዝ ሆነሽብኝ፤ ነፈዝ
ሂሳብሽን የማታኖሪ
መክሊትሽን ቀባሪ

ወርቅ ባፈር መንዛሪ
ብኩን ነጋዴ ሆንሽብኝ
ምንም ፋይዳ የማታፈሪ።
ፍቅርሽ እንዲያ ሲያስቀና
እንዲያ ሲነዝር ሲያቃጥል
ቀና ደፋ ሲያስብል፤
ክዳትሽ ደሞ ይብሳል
አለኝታን እንፉጭ ያደርጋል
መባውን ያለቅጥ ያሳሳል።
የሙት አንደበቱ
ጩኸትሽን ላይጮህልሽ
ወይ ላያንጎራጉርልሽ፤
የሙት ክንዱ
ላይጠልልሽ
ወይ ላያቅፍሽ፤
ሕይወቱ ነበር ያንቺ ፅናትሽ
ያንቺ ብርታትሽ።
ግን ለመላሽ መላ ልትነሺው
ለሌሊትሽ ኩራዙን ልትነፍጊው
ሲታደጉሽ ካልታደግሽማ
ሲኖሩልሽ ከገደልሽማ
በራስሽ የጨከንሽ አንቺ!
«ጥናቱን ይስጥሽ እማማ።»

# ውቤት

ብርሃን ነው አጥሯ ምሥራቅ እሮጎበርዋ
ጨረቃ በቀኝም ፀሐይ በግራዋ
በመሀሉ ያበራል እንደ እሳት መንበርዋ።
ምን ዓይነት ከያኒ ምን ይባል ኪነት
ፍጥረቷን ሸንትሮ በፀዳል ጥለት
እልፍኟን ቀጽሮ ባልማዝ ሰንሰለት
እንዳታውቅ ያረገ ጭለማ ዳፍንት
ምን ይባል ከያኒ ምን ይባል ኪነት?
እንደ ንጋት ጀምበር እንደ ሌሊት ጨረቃ
እንደ ራዕይ ምሣ እንደ ሕልም አበባ
የምድሪቱን ፍጡር ስትሰይ ስታባባ
መሆን አትችልና አንዲቱ ለሁሉ
ይኸንን ከዚያው ከመነጣጠሉ
ይበጀኛል ብላ ሠረገላ ብርሀን ቀርቦላት ተጭና
ወደ ሰማይ መንግሥት ሄደች በጥሞና።
እምላዕለ አርያም አርፋ በትስብዕት
ቀስተ ደመናውን ስትነድፍ ስትባዝት
ረገፉ መላእክት ወደቁ ሰማዕት
ገላቸውን ነካው የምድሪቱዝፍት።
ዳዊት በገፅዋ ላይ ቤርሣቤህን አይቶ
ሰቀቀው ገነቱ፣ ገሀነሙን ቃኘቶ ገሀነሙን ሽቶ

ፈለገ ፈቀደ ተመኘ እንደ ገና
ሊወድቅ ተትቢያ ሲጥለው ፈተና ሊጫነው ቀኖና።
‹ምንድን በጀኝ› አለ ‹ልቦ አምላክ መባሌ
ከሰማያት ጣራ ከመላእክቱ ጎራ እዚህ መሰቀሌ
ዞትር ለመዳከም ዞትር ለመታከት ለመምታት በገና
ጠዋት ሃሌ ሉያ ማታም ያው ምስጋና
በንእጉርጉሮ መድቀቅ በትካዝ መጫጨት ለእግዜር ለልና፤
ይሻለኝ ነበረ ካሁን ዘላለሜ የምድር ቅጽበቴ
ዐይኔ ያረፈበት የኦርዬን የእድሜ ልክ ፀፀቴ።›
ይህንን አድምጣ ፈርታ እንዳይናጋ የሰማይ መንግሥት
መሆኑ አስፈርቷት ቤተ - ሐዘን - ፀፀት
ሥጋ በለበሰው ብርሀን በጨፈቀው በላህይዋ ውበት
የሰማይ ኦዲሴ እንዳይኖር በመስጋት በሷ የተነሳ
ከምድር ተመለሰች፣ የዳዊት ጭንቀቱን እያሰላሰለች መልሳ መላልሳ።

# በለስ ለመለመች

ሕልም አይሉት ቅዠት

ሕልም አይሉት ቅዠት - ኑሮ አይባል ሞት

በባህላዊ ለኮ በልማድ ሰንሰለት

ስሳብ ስጎተት፤

የሸረሪት ድሬ እያፈተለከ

ዘሀው ተበጥሶ

ስቀጥል ስፈታ

ስፈታ ስቀጥል ዐይነስቤ ፈሶ፤

እንደው በደለማ ስቀመጥ ስነሳ፤

ራዕይ ቀረበኝ ልቤን የሚያሳሳ.....

«በለስ ለመለመች፤ በ. ለ. በ. ለ.

እያለ አወጋኝ

በቀኑ ደለማ ሌሊቱ ተጣባኝ።

በደካማ ጎኔ በድሁር መንፈሴ

ባካተተ ወኔ ባባከነ ቅርሴ

ምኑን ከምን ይገፍ፣ እንደምን አድርጌ

በለስን ልጠብቅ፣ ራሴን ታድጌ?

መለከት እምቢልታው ጨኸቱ ሰቀቀኝ

በነገ ዲብ ጮኸ ዛሬ አደነቀረኝ

ከዘመኑ ቀድሞ ዘመኔን ደሰምኝ።

ጊዜ ይሮጥ ጀመር ዛሬስ ወደ ኋላ

ከርሞ ይጋጭ ጀመር ከዛሬ ከለላ

ውሉዳነ ዘመን -

ይዋጉ ጀመረ ዛሬና ነጋቸው

በሰዎች ራስ ቅል፣ ደግሞም ባጥንታቸው።

ዛሬ አመድ መስሎ ነጥቶና ገርጥቶ

ከዐዋዩ ተፋቶ፣

የነገን ጨካኝ ክንድ፣ እሣት የለበሰ

ሲተባ ሲፈራ እየተላኮሰ፤

ሲዋጉ - ሲፋጩ ተግተው ሲዳሰሙ

እኔን ነው እሚመስል፣ ደማቸው ቀለሙ፤.......

ለዚህ ነው እሚያመኝ፣ ዘልቆም እሚወጋኝ

የነሱ መሸበር እንቅልፌን የነሣኝ

«በለስ ለመለመች» ራዕይ የገፋኝ።

# አይ መባከን

በዕረፍት

ዕረፍት እጦት ጣመን

መባነን

መመንመን

በዜሮ እንጀራ መቆነን

አይ መባከን።

ላንቀድስ ተከነን

ላናፈራ አብበን

አይ መባከን።

የዕድሜን ጩኸት

በሜዳ በቁም ቅዠት

በጓዳ በሴት ሙቀት

በሣሎን በአረቄ እጥበት

አይ መባከን

የምኞች ቦግ ቦግታ

የተስፋ ተግ ተግታ

ሲፈስ - መለስ ብሎ እብስ

ሲሮጥ - ዞር ብሎ መፈርጠጥ

አይ መባከን።

ፀደያችንን ድመድመን

ኮከባችንን አቃጥለን

ተንጫጭተንና ተዋዝተን

እኛው በእኛው አግጠን

ብቅ ብንል ካደባባይ

ግብሩን እንዳያቅ ተዋናይ

እምንለውን አናውቀው

እምናወቀውን አንለው።

በዘጥ - ረጥ

እየዳኹ መፍረጥ።
በጠብ - ረብ
ተወጥሮ መርገብ።
ሳናረጅ ተጡረን
ሣንዳር ገልሙተን
    አይ መባከን።
እቤት እኔ አቤት እናንተ!
ምናችን ይሆን ያለ
ምናችን ይሆን የሞተ?
በእረፍት
እረፍት እጦት ጣመን
    መባነን
    መመንመን
በዜሮ እንጀራ መቆነን
    አይ መባከን።

# ጉልበቴ በርታ፣ በርታ

እስቲ በሉ፣

ጉልበቴ በርታ በርታ

በሉ፤

በዛሬ ፃማችን ይታየን ስዕሉ፤

የነጋችን ድሉ።

ምፃተኛ ሥጋ፤ የራበው መንፈስ

የተቆረጠ አንጀት፤ አጎዳ ምላስ

የደካከመ ዐይን፣ የወየበ ጥርስ፣

ይታደስ ይለምልም፣ ያካላችን ዳሱ

በዛሬው ወዛችን፣ ነገን ለመካሱ።

ቢያንዘፈዝፈንም ክብደቱ የመስቀሉ

ቢጠይምብንም ዛሬያችን ፀዳሉ

ቢያንገዳግደንም የህላዌ ትግሉ፤

ለእምነታችን እምነት፣ ለተስፋችን ተስፋ

ከኛ ዘንድ አይመንን፣ ከኛ ዘንድ አይጥፋ።

ተራራው ኮረብታው፣ ሰማይና ምድሩ

መስኩ መልካው ወንዙ፣ ሸለቆና ዱሩ

ደኑ ጉራንጉሩ፣ ባህሩ ቆንጥሩ

ላህዩ እንዳይገፈፍ፣ እንዳይማስን መከኖ

ወዛችን ደማችን ይታደገው ፈጥኖ።

በመጋዝ በወስፌ በመንሽ በዋግንቦ

እጃችን ተፍታቶ ጠንክሮ ደልቦ፣

ዋልጌነት ከዕድሞአችን፣ ሥፍራ አጥቶ ተጣቦ፣

ማየት እንችላለን ዛሬ ነገን ጠርቦ

አንከዳ እንጂ እኛ፣ ተበዳዩን እኛ

ተፋጥነው ይመጣሉ፣ ዐለምና አዱኛ።

# ለምን ሞተ ቢሉ

ለምን ሞተ ቢሉ

ንገሩ ለሁሉ

ሳትደብቁ ከቶ፤

«ከዘመን ተኳርፎ

ከዘመን ተጣልቶ፤»

# ይቅርታ ለይቅርታ

ጎሊናዬ ያንጎራጉር ዐይኔ እንባ ያውርድ
በድያለሁና ጓደኛ ዘመድ፡፡
እንደ ፅኑ ቋጥኝ ጎርፍ እንዳይገፋው
ግጭትን ለመናቅ ፍቅር አቅም አለው፡፡
ግን ዶፉን እንደናቀ -
ለጣይ ለሙቀቱ እንዳልተጨነቀ -
እንደግሸር ቋጥኝ፣ በቀን ማዕበል፤
ቀን ባመጣው ሰበብ ፍቅርም ይወድቃል፡፡
ወዳጄ አትንፈገው ልብህን ብርሃን፤
ያስትውል መተከዝ ማልቀስ ማዘኔን፡፡
ራሴን ገፋሁት ጠላሁህ አሰኘኝ
ከእኔው ለመታረቅ አንተን አስፈለገኝ፡፡
ቅር መሰኘቴ በገዛ ፍጥረቴ፣
ሲያል መገንባት ነው በገነቱ ቤቴ፤
ብዬ ለይቅርታህ ምኔም መታከቴ፡፡
«በሠፈሩት ቁና.....» እንዳይሆን ነገሩ፤
ይሰማህ ወንድሜ ያሣቤ ምሥጢሩ፤
አቤት ባይ ሲመጣ -
ይቅር ላለ ማለት ጆሮህን እንዳትሰጥ፤
በርህን ስትዘጋ ጥሪው ውጪ ሲቀልጥ፤
አቤት ባይ ስትሆን ድምጥህ እንዳይቋረጥ፡፡

# የቋንቋ ሊቆቼ

የቋንቋ ሊቆቼ፤
ወረቀት በዋጡ
        በቦዘዙ ዓይኖቹ፤
ቃላት በሚረግጡ
        በደናሽ ከንፈሮች፤
ሲሉ ሰማኋቸው፤ -
«ቋንቋ መግባቢያ ነው
        ማለት ፍፁም ሐሰት
        ሊወጣ እሚችል
        ከማይም አንደበት
ይልቅስ እንጂ ነው
        ቋንቋ ያለ መግባቢያ
እንጨት ሲሉ በረድ በረድ ሲሉ ቋያ።
አሜን እንጂ አሜን
        ሌላማ ምን ይሏል?
ሰብአ ባቢሎንን
በሀያኛው ምዕት መፍረድ ያስቸግራል።

# በመላ ዕድሜያቸው

በመላ ዕድሜያቸው

በገማ አፋቸው

የሌላውን ሥጋ

ቆርጠው እሚያደቁ

እሚቦጫጭቁ

ለሰከንድ ቁርጥራጭ

ለደቂቃ ፍላጭ

ዘግተው አፋቸውን

ከፍተው ራሣቸውን

ትተው የውጭውን

ውስጡን ቢያስተውሉ

የልብን ጉድጓድ፤

በድማሜው ብቻ

ባደሩ በዋሉ

ቀሪ ዕድሚያቸውን

ሲያሙ ራሣቸውን።

# ለአንዲት ቅጽበት ብቻ

እስቲ የማነው ጉልበት

የሰው የአማልክት

ሊሰጠኝ እሚችል የደቂቃ ዕረፍት?

ከእውነት - ፍቅር - ውበት እማውወጋበት?

ለአንዲት ውብ ሙዚቃ ሀሣቤን ሰውቼ

ለአንዲት መልካም ቅኔ ባርነት ገብቼ

ህሊናዬን ቀልቤን፣ አካሌን ሰጥቼ

ለአንዲት ቅጽበት ብቻ!

የአ'ምሮዬ መርከብ ከማዕበል አምልጣ

ከሕይወት ስንክሣር አምርራ ፈርጥጣ

በዕፁብ - ውበት ቅኘት እጅግ ተመስታ ሌላው

ሌላው ነገር ባፍንጫዬ ይውጣ!

# ያላዋቂ ጠያቂ

ከመቼው

ከመቼው በል ጦነቸኸው?

የገደሉህን ልትገድል

የጣሉህን ልትጥል

ከመቼው በል ከመቼው ጦነቸኸው

ብለው፤

መቼ......መቼ ገና አየህና

ጉልበቴን ለካህና፤

ብሎኝ አለፍ እንዳለ

ከገን በላዬ ተጣለ።

# ከያኒና ኪነት

የከያኒው ዓይኑ

ምናቡ ብሌኑ

ጠየም የም እያለ

ጭስ እየመሰለ

መሄድ ከጀመረ

ያ ነው ምልክቱ

የግዘት የሞቱ።

የከያኒው ፍቅር

አይደለም - አይደለም

የብርሀን ፍቅር

በመለኮት ገላ

የእድፍ አበባ

ይልቅስ እንጂ ነው

የብርሀን ፍቅር

በጠላት አዝመራ
የሳምሶን ድብ ጭራ።
የከያኒው አንጎል
የገጠመኝ እህል
መሰለቂያ ጥርሱ
ከተፈናከረ ከተወናገረ
ያላመ ያልደቀቀ
ሽርክት ከለቀቀ
ምን ታከተ ጣረ
ምጣድ ላይ አደረ
ገል ሆነ
ሳይበላ ቀረ።
ከያኒና ኪነት
በቁርባን ጋብቻ
በትዳር ሠንሠለት
አብረው ይኖራል
አብረው ያፈጃሉ፤
አልፎ አልፎም ሲጣሉ
ከቶ ሳይለመን
ላይባባል ቅሉ
ውሉ ሳይጨበጥ
የሷ ወፈናፍራ
ከያኒ ይፋጠጣል

የፍቅሯን አልጀብራ

በወሲብ በሐሺሽ

በአረቄ በቢራ።

መቼም ያልተነካ

ግልግል አይገደው

ወይ ዘመድ ጓደኛ

ይህን ያስተዋለው

«ፍታት.......ሸሸ.......ራቃት»

ማለቱ አይከብደው፤

«እንደምን ይፋታል

እንደምን ይርቃል

ሰው ከገዛ ራሱ

እሷ እሱ - እሱ እሷ

እሱሷ እሷሱ»

ቢሉት መቸ ይገባው

ይረዳው መንፈሱ

አያ ሞኜ ሥጋ

አባ የዋህ ነፍሱ።

# በተረት ላሰላስል

መሬትና ጥንቸል ማኅበር ገቡና

ጽዋ ተጣጡና፤......

(ያው እንደዚያው ማለት)

ያጋጣሚ አይደል፤

የተፈጥሮ ባህል፤ የታሪክ ዘይቤ አለው አንድ ቋንቋ

አለው አንድ መላ

አንተና ልደትህን፣ አንተና ሀገርህን -

በማይረግብ ገመድ፣ ባንድ ላይ የቋጨ፤

ከዐፀደ ዘመን፤ ከቦታ ከለላ

በደም ቃልኪዳኑ ባንድ ያስተሳሰረ በማይታዩ

እጆች ባልተሰማ መሀላ።

እና፤

መሬትና ጥንቸል ማኅበር ገቡና

ጽዋ ተጣጡና -

መሬት የፈንታዋን ስትከፍል በጽሞና፤ -

(ያው እንደዚያው ማለት)

የሀገርህ ህይወት - የብዙኃን ሕይወት - ወዝ ደምና ቅስሙ

ብርታቱ ድካሙ - ተስፋውና ሕልሙ

ከእንቡጥ ወደ አበባ - ከአበባ እስከ ፍሬ - ለምልመህ ለማየት

በክንዶችህ ብርታት - በአዕምሮህ ንቃት -

በኀሊናህ ጥራት - ፀንተህ ለመመልከት

ዘንሚል በዘመናት - ወርዷል እንደዠማ - ፈሷል እንደ ጅረት።

እና፤

መሬትና ጥንቸል ማኅበር ገቡና ፅዋ ተጣቱና

መሬት የፈንታዋን ስትከፍል በጽሞና

እብስ አለች ጥንቸል፣ መክፈል ጠላችና፤.......

(ያው እንደዚያው ማለት)

በስንት ትላንት ነውና ዘንቦ ወይ ፀሀይቶ

በቁር ተኮራምቶ በዋዕይ ገርጥሞ

የበቀለ ዛሬ፤

ትውልድም ነውና፣ ያያት የቅድመ አያት

የእንዝላልት የእንጅላት

የመሠረት ፍሬ፤

በሺ እግሮች ተራምዶ ዛሬን የደረሰ ለእሱ እሱነቱ

በወቅቱ ለወቅቱ

ይኖር ወይ ደካማ የትውልድ እንክርዳድ

አደገኛ አዝመራ ከዚህ ከወጣቱ?

ማነው ይህ መጢቃ የፀደይ ቀን ዘመድ

ወጪቱን እሚሰብር፣ ዕዳውን እሚክድ

ከወገኑ እማይቆይ ከወገኑ እማይነድ?

የጫጩ መንፈሱ፤ የሽፈተ ሀሣቡ የከነፈ ልቡ

ራሱ መነሻው ደሞ ግቡ?

እና፤

መሬትና ጥንቸል ማኅበር ግቡና ፅዋ ተጣጡና

መሬት የበኩሏን ስተከፍል በጽሞና

እብስ አለች ጥንቸል፤ መክፈል ጠላችና፤......

ግና ምን ይሆናል?

ብትሮጠው ብትሮጠው ጋራውን ተሻግሮ፣

ሜዳውን አቋርጣ

አልቻለችም ከቶ፣ ከዕዳዋ ልትድን

ከመሬት አምልጣ።

# ባለቅኔዎች - (ከሎንግፌሎ የተተረጎመ)

ስሙኝ፤ እናንት ባለቅኔዎች

በዐፀደ ነብስ ያላችሁ፤

ደሞም በቅኔዎቻችሁ

ሕያውነት ያገኛችሁ

እናንተም ባለቅኔዎች ስሙኝ

በዐፀደ ሥጋ እያላችሁ

የሞታችሁ (ንቀት የሚገድል ቢሆን)

በእኩይ ዘመናችሁ ወቅት

ከእሾህ እክሊላችሁ ጭነት

ስትሰቃዩ በደም አበላ ጉርፈት

እንዴት ነው?

ደስ አይላችሁ

ተልእኮአችሁን ማድረሳችሁ?

አወን፣ የቅኔ ተውህቦ አግብሮቱ

መለኮታዊ ጣፋጭነቱ

የበደልን ምሬት ማጥፋቱ።

አይደል ባደባባይ ሕዝብ ጭብጨባ እልልታ፤

በመድብለ ሰብአ ውዳሴ አንደበት ሆሆታ፣

በእኛው ውስጥ እንጂ፣ ያለ አብሮን

ድል ለማድረግ ወይም ድል መሆን።

ፍርሃት አዶከብሬ

ፍርሃት አዶከብሬ

አያ እናት አይምሬ

የቁም መቃብሬ

የቅዠት ሀገሬ።

ከሥጋ ከነብሴ ከደሜ ቆንጥሬ

ከአጥንቱ ሰንጥሬ

ምስህን ሰጥቼ ላመልህ ገብሬ፤

ያው ነህ አንተ ግና

ልጓምህ አይላላ።

ትጋልበኛለህ በእሾህ በቆንጥር ላይ

ጨለማ እንደግራር በቅሎበት በሚታይ

አንዷት ዘሀ - ጮራ

በማትደፍርበት

እውነት - ፍቅር - ውበት

በተቀበሩበት።

# ኒሻን

ኒሻን
ዕፁብ ብርሀን
ትሁት ታጋይ
ጨለማን ያህል ፈያታይ
ቢጠለልም ካንቺው አምባ፣ አደባባይ
ካንቺው ሥጋ፣ ካንቺው ዐዋይ፣
ሰለባ አለጣለሽም ነበር፣ ግዳይ
ሽንፈት አልገባሽም ነበር ስቃይ
ጩኸት አልወጣሽም ነበር ብካይ።
ያይነሥጋን ሕፀፅ ድከምት
የጨለማን ግርዶሽ ጥለት
ገፈሽ በልቦና ብርሀን ውበት
ጥለሽ፣ በመንፈስ ፀዳል ፍመት
አልፈሽ፣ የቁም ሞትን ያህል ኬላ
ዘለሽ፤ የተስፋ - አልባን አጥር - ላባ፤
ተተግነሽ ከዕውቀት ምስካይ
ይህን ሕይወት ‹ሚሰኝ ቀላይ
የስንት ጎበዝ ትርክዛ አስጣይ
ተግተሽ ስትቀዝፊው ስናይ፤

ያን ሁሉ ትናት፤ ያን ሁሉ ብቃት
ያን ሁሉ ብርታት፣ ያን ሁሉ ምላት
እንዴት ብለን፣ መች ጠርጥረን
ሞት በድንገት ይነጥቅሻል በለን?
ኒሻን
ዕጹብ ብርሀን
ትሁት ታጋይ
ጨለማን ያህል ፈያታይ
ቢጠለልም ካንቺው አምባ አደባባይ
ካንቺው ሥጋ ካንቺው ዐዋይ
ሰለባ አልጣለሽም ነበር፣ ግዳይ
ሽንፈት አልገባሽም ነበርም ስቃይ
ጩኸት አልወጣሽም ነበር ብካይ።

# መንገደኛ

መንገደኛ
ልበመንታ ፈረሰኛ
ነገ አውላላ
ወይ አያልፉት ኬላ.....
ትላንት ብቻ
ትላንት ብቻ

ያለፉት ዘመቻ

ቆስሎ ደምቶ

ከስንት ግንባር ተጋጭቶ

ከስንት ከለቻ ተላትሞ

ከስትን ጥሩር ተዳስሞ

ደቅቆ ተዳስሞ

ደግሞ......አገግሞ

እንደ ጨረር ዘሀ ቀጥኖ

ከሮ

በጣት ስቁረት መሀል በሮ

ወይ እንደሾህ ተጠላልፎ

በስስ ስጋ መሀል አልፎ

ትላንት ብቻ

ያለፉት ዘመቻ።

ዛሬማ የነገ መባቻ

ቅርብ ድንበር - ሩቅ ዳርቻ

ቅርብ ድንበር - ሩቅ ጠፈር፤

ወይ የከእብሮ እስግምግምታ

የየቃጭል ቅጭልጭልታ

የመጋረጃ ኋላ ቱምታ።

ነገ አውላላ

ለሽምጥ ግልቢያ ቀና

ለሶምሶማ

እሚስማማ

ለድንገላሣ

ድንቅ ወላንሣ

ወይም

መሰናክል ኬላ

ገጣጣ ድንጋይ ከለላ

ጋሬጣ ጉድባ አሽከላ

መንገደኛዬ ሆይ

መንገደኛ

ትላንት አንጥፍና

ዛሬ ደርብና ተኛ

ጧት በበርህ በምድራኳ

የነገ ዛሬ እስኪያንኳኳ

# ተይው እንተወው

ተይው እንተውወ፤.......

የዘመን ቃፊሩን ማለፍ አልቻልንና

ይህ ዓለም ጥበቱ አለመጠነንና፤ -

ተይው እንተወው፤......

ውጥኑ ግብ ይሁን

ጅማሬው ፍጻሜ፣

ቅጽበቷ ሙሉ ዕድሜሽ

ወቅቷ ዘላለሜ።

# ብቻ ለሚያንሾካሹከው

ለቃል ኪዳኑ ነው

ለተልእኮው የሞተው

የማንም ልሣን

እንዲህ ነበር ለማይለው፤

ሐውልት አልባ መቃብሩ ላይ፤

የበቀለው

ሳር ስራስር ቅጠላቅጠል ብቻ፤

ለሚያንሾካሹከው......

እስከ ዘመን

ዘመን ዳርቻ።

# አባብዬ

አንተ ትሁት አንተ ቅን ሰው፤ አንተ ደግ ሰው

ቀኑ ቀን ካልሆነ በቃኝ.......አያሻኝም መኖር ብለኸው

እጆችህን ዘርግተህ፣ ሞትን ያህል እንግዳ ተቀበልከው ጨካኙ ፍጡር፣

እንደናፋቂ ወዳጅ ጨበጥከው።

......አባብዬ።

የትአል የሞት ወረንጦ ፍላፃው፤ ማራድ ማስፈራቱ

በል የትአል የሞት ሞትነቱ?

በንፁሕ ልቦና ብርታት በቤተሰብ አለኝታ

እምነት

ይዘልቋል ለካስ፣ እሚፈራው ዳገት......አቀበት።

.......አባባዬ።

ብዙ ነገር ብታውቅም፣ እማታውቃቸው አሉ

እኩይነት፣ ግብዝነት መኩራራትን የመሰሉ።

..........አባባዬ።

እውነትህ ነው ትዝታዬ.....አባቴ ብዙም

ተምሬአለሁ ከአንተ

እጅግ ብዙ እሲት ቢኖርም፣ ስንት ሊቃውንት

ያሚገተ

ቅንነትና እውነት እንደሁ፣ ዙሮ ዙሮ የሚረታ

ሰብዊነት እንደሁ ወሳኙ የሰው ልጅን ምፅአት የሚፈታ።

........አባባዬ።

# የክረምት ማገዶች

እንዲህ ተሜጭሰን

እንዲህ ተጨናብሰን

ውሀ እንዳለዘዘን

ከውሀ ተዋግተን ........ ተዋግተን.......ተዋግተን

ውሀው አሸነፈን፤

እሳትን ፀንሰን

እሳትን አምጠን......አምጠን.......አምጠን

እሳትንም ወልደን፣

እሳትንም ሁነን፤

(የክረምት ማገዶች)

ካጨለጨልንለት የድሃውን ጎጆ ቀዣ ከል ጭራሮ

ካበሰልንለት ዘንድ የአርሶ አደሩን ንፍሮ

የሰርቶ አደሩን ሕዝብ ለሰስ ያለ ሽሮ፤

ታሪክ ይዘምረው የኛን እንጉርጉሮ።

ዘመን ይመስክረው የኛን ውጣውረድ፤

የእንግልት ኑሮ።

# አይደለም (የዘወትር ምጤ)

አይደለም ለክብረት ለንዋይ ተዳምሮ
አይደለም ለሹመት ለተጫፍሮ ኑሮ
አይደለም ለዝና ለጠፊ ውሎ አድሮ፤.......

ለትሁት ሕይወት ነው፤ እኔ መሯሯጤ
በዘልማድ መንገድ ጉዞ አለመመረጤ፤

ደቂቅ ብርሃንን -
ውበት - ፍቅር - እውነትን


ለመገላገል ነው፤ የዘወትር ምጤ።

ይኸው ነው መስቀሌ
ይህም ነው አክሊሌ

ይኸው ነው ድከሙቴ
ይህም ነው ብርታቴው

# ጊዜ በረርክ በረርክ

ጊዜ በረርክ በረርክ
ጊዜ በረርክ በረርክ
ግና ምን አተረፍክ
ግና ምን አጎደልክ?
ሞትን አላሸነፍክ
ሕይወትን አልገደልክ።



# ስለደራሲው በጥቂቱ

በሲዳሞ ክፍለ ሀገር ይርጋዓለም ከተማ ሐምሌ 5 ቀን በ1942 ዓ.ም. ተወለዱ፡፡ የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን የርጋለም ከተማ በሚገኘው በራስ ደስታ ትምህርት ቤት የተማሩ ሲሆን ሁለተኛ ደረጃን በኮከበ ፅባሕ አዲስ አበባ ውስጥ ተከታትለዋል። የከፍተኛ ትምህርታቸውን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመከታተል በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ የመጀመሪያ፣ በእንግሊዝኛ ሥነ ጽሑፍ ደግሞ የሁለተኛ ዲግሪያቸውን አግኝተዋል፡፡

በአጫጭር ድርሰት በግጥምና በቴያትር እንዲሁም በሂስ ሥራቸው በብዙዎች ዘንድ የሚታወቁት ደበበ ሰይፉ የሀገሪቱ የሥነ ጽሑፍ እድገት ከፍተኛ ደረጃ እንዲደርስ ጥረት ያደረጉ ምሁር ነበሩ፡፡ በ1966 ዓ.ም. "ሣይቋጠር ሲተረተር" የሚል ድራማ ጽፈው በኢትዮጵያ ቴሌቭዥን ታይቷል፡፡

"የብርሃን ፍቅር" በሚል ርዕስ ያሳተሙት ቁጥር 1 እና ቁጥር 2 የግጥም ስብስብ መጻሕፍታቸው ብዙዎች ዘንድ አድናቆት አትርፈዋል፡፡

**ምንጭ:** የኢትዮድያ ደራሲያን ማህበር ለሚሊኒየም ያሳተመው አጀንዳ።

## <u>የደራሲው ሥራዎች</u>

1. የብርሃን ፍቅር (**ግጥምና ቅኔ**)
2. ለራስ የተፃፈ ደብዳቤ (**ግጥምና ቅኔ**)
3. ከባሕር የወጣ ዓሣ (**ተውኔት**)